በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ የጉለሌ ክፍለ ከተማ ት/ጽ/ቤት በ2016 ዓ.ም የትምህርት ዘመን የሁለተኛ ወሰነ ትምህርት ለ6ኛክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀ የአማርኛ ቋንቋ ሞዴል ፈተና

- **የተፈቀደ ጊዜ 1፡00 ሠዓት**
- **የጥያቄ ብዛት፡40**

መመሪያ፡-

- **ይህ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ጥያቄ ብዛት 40 ሲሆን የተሠጠው ጊዜ 1 ሠዓት ነው፤ ከተሠጠው ሠዓት ውጪ መሥራት አይቻልም፡፡**
- **መኮራረጅ ወይም የፈተና ሕግ የማያከበር ፈተናው አይያዝለትም፡፡**
- **እያንዳንዱን ጥያቄ አንብባችሁ ትክክል መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ በመልስ መስጫው ወረቀት ላይ በአግባቡ አጥቀሩ፡፡**

ምንባብ

የአሸንዳ ጭፈራ

የአሸንዳ ጭፈራ ከነሀሴ 16 እስከ 19 ባሉ ሶስት ተከታታይ ቀናት ይከበራል።

በዓሉ በዋነኝነት የልጃገረዶች በዓል ነው። ትዳር የመሠረተች በአሸንዳ ጭፈራ አትሳተፍም።

በዓሉ የመስክ በዓል በመሆኑ የአሸንዳ ሴቶች የትዋላችሁ ተብለው የማይጠየቁበት ብርቅዬ እና የነፃነት ቀናቸው ነው። የአሸንዳ በዓል ፍቅራቸውን የሚገልፁበት፣ መንደራቸውን የሚያደንቁበት አባቶቻቸውን እና እናቶቻቸውን የሚያከብሩበት ህዝባዊ በዓል ነው።

ለበዓሉ ውስን ቀናቶች ሲቀሩ ሴቶች ቡድን ይመስርታሉ። ቡድኑ ከአብሮ አደግ ልጃገረዶች ይዋቀራል። ሴራ-ሚዜ ይባላሉ። ሴራ-ሚዜዎች የሚወጡ ዘፈኖችን ይቀበላሉ።

ምንጭ፡- ክብሮም አሰፋ ሞላ 2005ዓ.ም የራያ ህዝብ ባህልና ታሪክ

ከገፅ137-140 የተወሰደ

መመሪያ አንድ፡- <u>ከላይ የቀረበውን ምንባብ መሠረት በማድረግ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ ስጡ፡፡</u>

1. የአሸንዳ በዓል መቼ ይከራል?

ሀ. ከመስከረም 1 እስከ ጥቀምት 15 ሐ. ከሰኔ 12 እስከ ነሀሴ 1

ለ. ከነሀሴ 16 እስከ ነሀሴ 19 መ. ከግንቦት 1 እስከ ሰኔ 3

2. "ብርቅየ" የሚለው ቃል በምንባቡ መሠረት አውዳዊ ፍቺው ምንድ ነው?

ሀ. ቆንጆ ፊት ለ. ልዩ ቀን ሐ. ብርቅርቅ መ. የማያስፈልግ ቀን

3. ከዚህ ቀጥሎ ተዘበራርቀው የቀረቡትን ዓ/ነገሮች ተስተካክለው ሲፃፉ የሚያሳየው የቱ ነው?

1.ቁርሴን ሳልበላ ተጣድፌ ከቤት ወጣሁ፡፡

2. ከዚያም መምህሩ አንበርክኮ ቀጣኝ፡፡

3.የት/ቤቱ የሰልፉ ስነስርዓት አልቆ ደረስኩ፡፡

4. ከእንቅልፌ አርፍጄ ተነሳሁ፡፡

ሀ. 4፣1፣3፣2 ለ. 3፣4፣2፣1፣2 ሐ4፣3፣1፣2 መ. 1፣3፣2፣4

4. ራሱን ችሎ መቆም የሚችልና ትርጉም የሚሰጥ አነስተኛ የቋንቋ ክፍል ምን ይባላል?

ሀ.ሀረግ ለ ነፃ ምዕላድ ሐ. ጥገኛ ምዕላድ መ. አንቀፅ

5. በዛሬው ዕለት <u>አቤል</u> ወደ አዲስ አበባ ገባ፡፡ በዚህ ዓ/ነገር የተመሰረተበት ስም ---- ነው?

ሀ. እምር ለ.የውል ስም ሐ. የተፀውኦ ስም መ. ቅፅል

6. "ዘመን -ኦዊ-ነት "በሚል ተነጣጥሎ የቀረበውን ቃል ቅጥያዎችን በማጣመር ሲመሠረት ---------- ይሆናል

ሀ.ዘመናዊነት ለ. ዘመናዊት ሐ. ዘመናት መ.ዘመናዊ

7. "ጎመጀ" ለሚለው ቃል ተመሳሳይ ፍቺ የቱ ነው?

ሀ. ጓጓ ለ. መታ ሐ. ቋመጠ መ. ሀ እና ሐ መልስ ናቸው

8.እናቴ ዛሬ ከሱቅ ደብተር___መጽሐፍ_____እርሳስና ብዕር ገዛችልኝ፡፡

በዚህ ዓ/ነገር ውስጥ ባዶ ቦታውን የሚያሟላ ስርዓተ ነጥብ የቱ ነው?

ሀ.ሁለት ነጥብ ለ. አራት ነጥብ ሐ. ነጠላ ሠረዝ መ. ድርብ ሠረዝ

9. በሀገራችን በርካታ ወራጅ ወንዞች አሉ፡፡ በዚህ ዓ/ነገር ውስጥ የወል ስም የሆነው የቱ ነው?

ሀ. ወራጅ ለ. ወንዞች ሐ.አሉ መ. በርካታ

10. ከሚከተሉት ውስጥ የወል ስም የሆነው የትኛው ነው?

ሀ.ጎንደር ለ. ኤርሚያስ ሐ. እፅዋት መ. ሀዋሳ

11. የቃላዊ ግጥም ፋይዳ የሆነው የትኛው ነው?

ሀ. የማህበረሠብ ወግ እና ባህልን በቃል ያስተላልፋል፡፡

ለ. የማህበረሠቡን ወግ ባህል አይገልፅም፡፡

ሐ. በፅሑፉ ይተላለፋል፡፡

መ.ግጥሙ ከትውልድ ትውልድ አይተላለፍም፡፡

12. ሐምሌ ነሀሴ ያልተራበ ሰው፣

ሞፈር ቀንበሩን ---------- ቃላዊ ግጥሙን የሚያሟላው ሀረግ የቱ ነው?

ሀ.ፈልጦ ይማግደው ለ.ቀሚስ ያልበሰው ሐ. ገደል ይከተተው መ. ቅቤ ይቀባው

13. “አሰቃቂ” ለሚለው ቃል ተቃራኒ ፍቺ የሚሆነው የቱ ነው?

ሀ.አሣዛኝ ለ. አስደንጋጭ ሐ. አዝናኝ መ. አድካሚ

14. እዝባር(/) የዚህ ስርዓተ ነጥብ አገልግሎት ምንድ ነው?

ሀ. ቃልን አስጥሮ ለመፃፍ ሐ. የደብዳቤ ቁጥር ለመፃፍ

ሐ. ቀን እና ዓመተ ምህረትን ለመለየት መ. ሁሉም

15. አንድ ነገር መቼ እንደተከሰተ ወይም እንደሚከሰት የሚገልፅ የግስ አይነት የቱ ነው?

ሀ. ስም ለ. የጊዜ ተውሳከ ግስ ሐ. ቅፅል መ. መስተዋድድ

16. የአሸንዳ በዓል በዋነኝነት የሚሳተፉት እነማን ናቸው?

ሀ. ሽማግሌዎች ለ. እናቶች ሐ. ልጃገረዶች መ. ህፃናት

17. “አሚኬላ” ለሚለው ቃል ተመሳሳይ ትርጉም የሚሆነው የቱ ነው?

ሀ. ችፍርግ ለ. ጨካኝ ሐ. እሾህ መ. ስንደዶ

18. “ርባፀትገያህ” ይህ ትርጉም የማይሠጥቃል ትርጉም በሚስጥ መንገድ ሲገጣጠም የቱን ይመሠርቷል ?

ሀ.ገፀ ባህር ለ. ገፀ ባህርያት ሐ. ባህረ ገፅ መ. ህፀ ባህር

19. በመቀጠል ተዘበራርቀው የቀረቡትን ዓረፍተ ነገሮች ተሰተከክለው በአንቀፅ ሲፃፍ

1. ከዚያም አጣዳፊ ምጥ ይዘት በጣር ማጉረምረም ጀመረ

2. ድንገት ሣይታሠብ ሰማዩ በጥቁር ደመና ተሸፈነ።

3.ጉርምርምታው ብዙም ሣይቆይ ዶፍ ዝናብ ወረደ።

4. ሰዎቹም ጉዟቸውን ትተው በቅርብ ወደ ሚገኝ መጠለያተጠጉ።

ሀ. 2፣1፣3፣4 ለ. 3፣4፣1፣2 ሐ. 2፣3፣4፣1 መ. 1፣3፣4፣2

20. አለሚቱ በሚቀጥለው አመት ትመጣለች። ይህ ዓ/ነገር የተመሰረተው በየትኛው የጊዜ ግስ ዓይነት ነው?

ሀ.ሀላፊ ጊዜ ለ. የአሁን ጊዜ ሐ. የትንቢት ጊዜ መ. የዋህ ሀላፊ

21. “የአንድነት ፓርክ የበርካታ ጐብኝዎችን ቀልብ የሚሰብ ነው።” ሲል ምን ማለቱ ነው?

ሀ. የሚማርክ ለ. የሚጐትት ሐ. የማያስደስት መ. የሚያስጠላ

22. በሃላፊ ጊዜ የተፃፈው ዓ/ነገር የትኛው ነው?

ሀ. ወደ ሰባተኛ ክፍል አልፋለሁ። ሐ. ለሽርሽር ወደ ሀዋሳ ሄጀ ነበር።

ለ. ዛሬ ፈተና እየተፈተንኩ ነው። መ. ፈተና ጨረሼ ወደ ቤት ሄድኩ።

23. “መሠላል” ለሚለው ቃል ፍካሬያዊ ፍቺ የሚሆነው የቱ ነው?

ሀ. ዱላ ለ. አጭር ሐ. ወፍራም መ. ረጅም

24. አለሙ ነገ ከሀዋሳ ---------- ። ይህንን ዓ/ነገር ትክክለኛ የጊዜ ግስን ሊያሟላ የሚችለው የቱ ነው።

ሀ. መጣ ለ. ሊመጣ ሐ. ይመጣል መ. መጥቷል

25. “መከራት” በሚለው ቃል የተጨመረው ድህረ ግንድ ቅጥያ የቱ ነው?

ሀ. -ች ለ. - ኡት ሐ. - ኡ መ. - ኣት

26. በዝርው የሚነገር የስነቃል ዓይነት የቱ ነው?

ሀ. ፍከራ ለ. ተረት ሐ. የልጆች ጨዋታ መ. ሙሾ

27. እማሬያዊ ፍቺ የሚያሳየው ዓ/ነገር የቱ ነው?

ሀ. ሰለሞን በትምህርቱ እሳት ነው። ሐ. ዘምዘም በርበሬ ለማዘጋጀት ኮሪሪማ ገዛች።

ለ. ሮዛ ምስጥ ናት። መ. ሚኪያስ ቆቆ ነው።

28.አንድ ቃል በቀጥታ ከሚኖረው ፍቺ ባሻገር ሚስጥራዊ ፍቺ ሲኖረው ምን ይባላል?

ሀ. ፍካሬያዊ ፍቺ ለ. ተመሳሳይ ፍቺ ሐ. እማሬያዊ ፍቺ መ. አንቀፅ

29. ቀኑ መሸቷል፤ --------- ወደ ቤታችን እንግባ! ባዶ ቦታው የሚገባው አያያዥ የቱ ነው?

ሀ. በተጨማሪ ለ. ስለዚህ ሐ. ወይም መ. ከዚያም

30. አበበ የቤት ስራውን ስራ። በዚህ ዓ/ነገር አበበን የሚተካው ተውላጠ ስም የቱ ነው?

ሀ. እኛ ለ. እነሱ ሐ. እናንተ መ. እሱ

31. ከሚከተሉት አማራጮች ውስጥ ስለ አንቀፅ ትክክል የሆነው የቱ ነው?

ሀ. አንድ ዋና ሀሣብ ይይዛል። ሐ. በውስጡ የተለያዩ ሀሣቦችን ይይዛል።

ለ. የሀሣብ አንድነት አይኖረውም መ. ግጥምጥምነት የለውም።

32. የጥላቻ ንግግር መከላከል የሚቻለው እንዴት ነው?

ሀ. ከሀሠተኛ መረጃ በመቆጠብ ሐ. በመቻቻልና በመከባበር

ለ.የሌሎችን ባህልና እምነት ማክበር መ. ሁሉም

33. አለማየሁ ለንግድ እንደ ወጣ <u>የውሃ ሽታ</u> ሆኖ ቀረ። የተሰመረበት ቃል አገባባዊ ፍቺ የቱ ነው ነው?

ሀ. የተሠማ ለ. ደብዛው የጠፋ ሐ. የተገኘ መ. የታወቀ

34. ቀጥሎ ከተዘረዘሩት ዓ/ነገሮች መካከል ውስብስብ ዓ/ነገር የቱ ነው?

ሀ. አስቴር ልብስ አጠበች። ሐ. ግቢው ተከፍቷል።

ለ. ተማሪው እጁን ታጥቦ ምሳው በላ። መ. እንግዶቹ ቀሩ።

35. ከሚከተሉት ውስጥ ባህሪ አመልካች ቅፅል የሆነው የቱነው?

ሀ. ደግ ለ. ወፍራም ሐ. ጥቁር መ. ጠፍጣፍ

36.የሚከተሉትን ሀሣቦች በማንበብ በሀቅ ላይ የተመሠረተው አስተያየት የቱ ነው?

ሀ. በሚቀጥለው ሳምንት ሳልመጣ አልቀርም።

ለ. በፈተናው ጥሩ ውጤት የሚመጣ ይመስለኛል።

ሐ. ፀሀይ በስተምስራቅ ትወጣለች።

መ. የሽንኩርት ዋጋ በሚቀጥለው ወር ሳይቀንስ አይቀርም።

37. “ህቡዕ” ለሚለው ቃል ተቃራኒ ፍቺ --------- ነው?

ሀ. ድብቅ ለ. ገሀድ ሐ. ስውር መ. የማይታይ

38. --------- ግለሰቦች ወይም ቡድኖች ጎራ ለይተው የሚያካሂዱት የሀሣብ ፍጭት ወይም ሙግት ነው።

ሀ. ውይይት ለ. ጭውውት ሐ.ዘገባ መ. ክርክር

39. --------- የክርክር አተገባበር መርሆዎች ከሆኑት ውስጥ አንዱ ነው?

ሀ. እርግጠኛ ሆኖ ማቅረብ ሐ. ግልፅ አለመሆን

ለ. ስሜታዊ መሆን መ. የተዛባ መረጃ መስጠት

40. ድርጊቱ በባለቤቱ ላይ የሚፈፀም መሆኑን የሚያሳይ የግስ ዓይነት-------- ይባላል።

ሀ አሳቢ ግስ ለ. ሳቢ ግስ ሐ. ተውላጠ ስም መ. ስም